Summer RISE
Connecting Students to Careers

# Summer RISE 2021 Student Agreement
# ሠመር ራይዝ 2021 የተማሪ ስምምነት

Partnerships Unit
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
45 West Gude Drive, Room 2301, Rockville, Maryland 20850

## የወላጅ/ሞግዚት/ብቁ ተማሪ ስምምነት (PARENT/GUARDIAN/ELIGIBLE STUDENT CONSENT)

ሠመር ራይዝ 2021 ፕሮግራም የተነደፈው በአሁኑ ወቅት በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ለሚማሩ ራይዚንግ ጁንየሮች እና ለሲንየሮች በሠመር 2021 የሙያዊ ትምህርት እድሎችን ለመስጠት ነው። ለሠመር ራይዝ ፕሮግራም ስመዘገብ፣ በ 2021-2022 የትምህርት ዓመት በ MCPS 11ኛ ክፍል ጁንየር ተማሪ ወይም 12ኛ ክፍል ሲንየር ተማሪ ስለምሆን ብቁ እንደሆንኩ በማረጋገጥ ነው። በሠመር ራይዝ ፕሮግራም/Summer RISE Program ስሳተፍ ከወላጅ/ሞግዚት ጋር በአንድነት ሙሉ ኃላፊነት ወስጄ ነው።

1. ተገንዝቤአለሁ:- የሠመር ራይዝ ፕሮግራም "Summer RISE Program" ተሳታፊ እንደመሆኔ መጠን፥ እዚህ ላይ እንደተገለጸው በሣምንት 10 ሠዓት እና በቀን ከ 8 ሠዓት የማይበልጥ ጊዜ፥ እንዲሁም በሣምንት ከ 30 ሠዓት ለማይበልጥ ጊዜ፥ በጠቅላላ በአራት ሣምንት ውስጥ ከ 40 እስከ 60 ሠዓት በተመደብኩበት ቢዝነስ፥ ድርጅት፥ ኤጀንሲ፥ ተቋም ወይም (my "Career Experience Host") የሥራ ቦታ ላይ ወይም ቨርቹወል እየሠራሁ በመሣተፍ የሙያ ልምምድ ትምህርት ("Career Experience") እድል እንደማገኝ ተረድቻለሁ። የሙያ ልምምድ ጁላይ 5/2021 ተጀምሮ በሣምንት እስከ አምስት ቀን፥ ለአራት ሣምንት ይሠራል። ጁላይ 30/2021 ይጠናቀቃል።
2. ተገንዝቤአለሁ:- ለሠመር ራይዝ ፕሮግራም/Summer RISE Program ከመመዝገቤ በፊት ለሠመር ራይዝ ቡድን የሙያ ሥራ ልምድ ምደባ እንዲያመች የራሴን ሦስት ዋና ዋና የሙያ ምርጫዎቼን ለይቶ ለማወቅ በ Naviance የሚሰጠውን "the Career Interest Profiler እና the Career Cluster Finder" መውሰድ አለብኝ።
3. ተገንዝቤአለሁ:- በሠመር ራይዝ ፕሮግራም "Summer RISE Program" ለመሣተፍ፥ የወላጅ/ሞግዚት ስምምነት ማረጋገጫ መስጠት እንዳለብኝ እና ቨርቹወል ፕሮፌሽናል ክህሎት እና የፋይናንሻል ሊተረሲ አውደጥናት/ዎርክሾፕ መሳተፍ እንደሚጠበቅብኝ ተረድቻለሁ። የስልጠናው ዝርዝር በኢ-ሜይል እንደሚላክልኝ ገብቶኛል።
4. ተገንዝቤአለሁ:- እኔ በአካል የሙያ ልምምድ ማድረግ ካለብኝ፥ የሙያ ልምምድ እስከምወስድበት ቦታ ድረስ የመጓጓዣ ኃላፊነቱ የራሴ መሆኑን ተረድቻለሁ። (ከ 5–18 እድሜ) ያላቸው ተማሪዎች በሙሉ በሞንትጎመሪ ካውንቲ "Youth Cruiser SmarTrip card" በመጠቀም Ride On፥ Ride On Flex፥ እና አንዳንድ Metrobus መስመሮችን በነፃ ለመጠቀም ይችላሉ። የስማርት ትሪፕ ካርዶች "SmarTrip cards" ማመልከቻ በ "my school" እና በሌሎች ስፍራዎችም ይገኛል። ስለ "Youth Cruiser SmarTrip card" ተደራሽነት የበለጠ መረጃ ለማግኘት፥ "my College/ Career Information Coordinator" ማግኘት አለብዎት እና/ወይም ይህንን የሞንትጎመሪ ካውንቲ ትራንስፖርቴሽን ዲፓርትመንት ድረገጽ ይጎብኙ:- www.montgomerycountymd.gov/DOT-Transit/kidsridefree/።
5. ተገንዝቤአለሁ:- የሙያ ልምምድ ምደባ የሚደረገው በእኔ የሙያ ፍላጎት፣ በመልክዓ ምድራዊ መኖርያ አካባቢ፣ በአካል፣ እና/ወይም ቨርቹወል ምርጫዬን መሠረት በማድረግ የመገኘቱ ሁኔታ የሚወሰን መሆኑን ተረድቻለሁ።
6. ገብቶኛል:- የሠመር ራይዝ ፕሮግራምን "Summer RISE Program" በሚመለከት ወቅታዊ መግለጫ ለእኔ ኢ-ሜይል እንደሚደረግ እና "non-MCPS እና የ MCPS ኢ-ሜይል" አድራሻዎቼን ከሠመር ራይዝ ጽ/ቤት (Summer RISE office) ከተነገረኝ በኋላ በየቀኑ ማየት-መከታተል እንዳለብኝ ተረድቻለሁ።
7. ተገንዝቤአለሁ:- የእኔን መርኃግብር በሚመለከት ከሙያ ልምምድ ተቀባይ የሚመለከተው ሠራተኛ(ኞች) ወይም ተወካይ (my "Career Experience Host Designee(s)") ጋር በቀጥታ የማስተባበር ኃላፊነት እንዳለብኝ ተረድቻለሁ።
8. ተስማምቻለሁ:- በጥሩ ሁኔታ ለመከታተል፥ ጥሩ ስነምግባር፥ ትክክለኛነት፥ ሥነ ሥርዓት፥ በፍጥነት፥ በአስተዋይነት፥ ተገቢ አለባበስ፥ እና አግባብ የሆነ የቢዝነስ ስነ-ምግባር እና ቨርቹወል የምሳተፍ ከሆነ፣ ቪድኦ ላይ መሆን እንደሚጠበቅብኝ ተስማምቻለሁ። በ "my Career Experience Host Designee(s)" አማካይነት የማይፈታ ጉዳይ ካጋጠመኝ ወይም አሳሳቢ ሁኔታ ካለ ወደ "my Summer RISE teacher liaison" ወይም ለ "MCPS Summer RISE Program office" በኢ-ሜይል:- summer-rise@mcpsmd.org ወይም ቁጥር 240-740-5599 በመደወል አሳውቃለሁ።
9. ገብቶኛል:- የሥራ ልምድ የሚሰጠኝ ድርጅት ተጨማሪ የምልመላ መስፈርቶች ለኖረው ስለሚችል፥ ጁላይ 5 የሠመር ራይዝ ፕሮግራም/Summer RISE Program ከመጀመሩ በፊት የምልመላ መስፈርት ለማሟላት የሚያስፈልጉ ማናቸውንም ተጨማሪ ነገሮች በቀጥታ ከ "my Career Experience Host Designee(s)" ጋር መሥራት የራሴ ኃላፊነት ነው።
10. ተረድቻለሁ:- የሥራ ልምድ ለሚሰጠኝ ድርጅት/my Career Experience Host ተቀጣሪ አለመሆኔን። የሥራ ልምድ የሚሰጠኝ ድርጅት/My Career Experience Host ከሠመር ራይዝ ተሳታፊዎች ወዲያውኑ የሚያገኘው ምንም አይነት ጥቅም እንደሌለ፣ እና አንዳንዴ ሥራቸው እንኳ ሊደናቀፍ እንደሚችል፥ የሙያ ልምምድ በሚሰጠኝ ድርጅት/my Career Experience Host የእለት ተእለት ሥራ ውስጥ (ፋይል ማድረግ፣ ሌሎች የጽሕፈት ሥራዎችን ማከናወን፣ ወይም ደንበኞችን መርዳት) በመሣሠሉት ተግባሮች በመደበኛነትም ሆነ ወይም በተከታታይ በቀጥታ እንደማልሰማራ ተገንዝቤያለሁ። የእኔ የሙያ ልምምድ ሰጪ ተወካይ(ዮች) "My Career Experience Host Designee(s)" የቢዝነስ/የድርጅቱን አጠቃላይ እንቅስቃሴዎች የሚያመለክት መግለጫ ይሰጡኛል፥ እና የእኔን ሚና፥ ኃላፊነቶች፥ እና ለቢዝነሱ/ለድርጅቱ ማከናወን ያለብኝን ተግባሮች ያስተምሩኛል። ለሥራ አስፈጻሚው(ዋ) ወይም ማኔጀር ዉጤታማ በሆነ መንገድ ለመከወን የሚረዳ ጥራት፣ ክህሎቶች፣ እና እውቀትን በጥልቀት በመሻት እነዚህን ተግባራት እፈጽማለሁ። በበርካታ የሥራ ቅጥር አካባቢዎች ላይ መጠቀም የምችለዉን ሙያዎች ለመማር እድል ይኖረኛል።
11. ተስማምቻለሁ:- የአጋማሽ ጊዜ እና በፕሮግራሙ መጨረሻ ላይ ስለ ሠመር ራይዝ ፕሮግራም "Summer RISE Program" የዳሰሳ ግብረመልስ ለማቅረብ ተስማምቻለሁ።

12. **በመገንዘብ ተስማምተዋል:-** የሠመር ራይዝ ፕሮግራም "Summer RISE Program" ተሣታፊዎች $300 አበል ያገኛሉ፥ ፈንዱ እንደተገኘ፣ ፕሮግራሙን በተሳካ ሁኔታ ካጠናቀቁ በኋላ ለፕሮግራሙ ያወጡትን ወጪ ለማካካስ በኤሌክትሮኒክስ ቀጥታ ዲፖዚት ይደረጋል። እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሠመር ራይዝ " Summer RISE Program" ከተጠናቀቀ በኋላ ፈንዱን ለሚያስተዳድረው ባንክ የእኔን የመጀመሪያ እና የመጨረሻ ስም ያስተላልፋል። ቀደም ሲል ከባንክ ተቋም ጋር የተከፈተ አካውንት ከሌለኝ፥ ፈንዱን በሚያስተዳድረው ባንክ ወይም እኔ በመረጥኩት ባንክ አካውንት የመክፈት እድል ይኖረኛል። የሚሰጠኝን አበል ቀጥታ ዲፖዚት የሚደረግበት ቅጽ ሞልቼ መስጠት እንዳለብኝ ይጠበቅብኛል። የባንክ አካውንት ለመክፈት የተለየ አዳጋች ሁኔታ ከተፈጠረ፥ እኔ በምማርበት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የኮሌጅ ወይም የሙያ መረጃዎች አስተባባሪ "College/Career Information Coordinator"፣ "my Summer RISE teacher liaison" ወይም የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ጽ/ቤትን "Summer RISE Program office" በኢሜይል summer-rise@mcpsmd.org ወይም የስልክ ቁጥር 240-740-5599 በመደወል አሳውቃለሁ።

13. **ገብቶኛል:-** በሠመር ራይዝ ፕሮግራም "Summer RISE Program" መሣተፌ የሙያ ልምምድ ካደረኩበት ተቋም (my Career Experience Host) ሥራ የማያሰጠኝ መሆኑን እና በሠራተኝነት ለመቀጠር መጠበቅ እንደሌለብኝ ተረድቻለሁ።

14. **ተረድቻለሁ:-** በሠመር ራይዝ ፕሮግራም "Summer RISE Program" ወቅት ቪድኦ ቴፕ እንደሚደረግ፥ ፎተግራፍ እንደሚነሣ፥ እና/ወይም ሪኮርድ እንደሚደረግ ገብቶኛል። እነዚህ ምስሎች እና/ወይም ሪኮርዶች ስለ ሠመር ራይዝ "Summer RISE" ለማስተዋወቅ እና ምስሎቹ ያለተጨማሪ መግለጫ ለተለያዩ ዓላማዎች ጥቅም ላይ እንደሚውሉ ተስማምቻለሁ። በእነዚህ አጠቃቀሞች ምክንያት ምንም ክፊያ እንደማይሰጠኝ እና ምስሎቹ፣ ቪድዎች፣ ሪኮርዶቹ፣ እንዲሁም ማናቸውም በዚህ መነሻ ምክንያት የሚፈጠሩ ሥራዎች ባለቤትነቱ የ MCPS መሆኑን እገነዘባለሁ።

15. **ተገንዝቤአለሁ:-** የእኔ የሥራ ልምምድ ተቀባዬ ተወካይ(ዮች) ስለ እኔ የሥራ ልምምድ ተሳትፎ ከ MCPS ጋር መረጃ እንደሚለዋወጡ ተረድቻለሁ። የእኔ የሥራ ልምምድ ተቀባይ ወይም ተወካዩ ስለ ሠመር ራይዝ ፕሮግራም "Summer RISE Program" ተሳታፊዎች ከማናቸውም ሌላ ሦስተኛ ወገን ጋር መረጃ አይለዋወጥም።

16. **ተረድቻለሁ:-** በ "my Career Experience Host" አማካይነት በዚህ ስምምነት ላይ የተጠቀሱ ህጎችን እና ደምቦችን/መመሪያዎችን፥ ወይም ማናቸውንም ሌሎች የሠመር ራይዝ ፕሮግራም "Summer RISE Program" ደምቦችን ስላከብር ብገኝ፣ ከሠመር ራይዝ ፕሮግራም "Summer RISE Program" እንደምወገድ እና የ $300 አበል እንደማላገኝ ተገንዝቤአለሁ።

17. ስለ ሙያ ልምምድ **የሚያሳስበኝ ነገር ካለ:-** በፍጥነት ወደ "my Summer RISE" አስተማሪ ለያዘን ወይም ለ "Summer RISE Program office" በይነመረብ ላይ summer-rise@mcpsmd.org ወይም 240-740-5599 በመደወል ሪፖርት ይደረጋል።

ስለ "Summer RISE 2021 Student Agreement" የተማሪ ስምምነት ለማመልከት በመመዝገቢያ ቅጽ ባለዉ ሳጥን ላይ ምልክት እንዲያደርጉ ይገለጻል፣ እናም ይህ በኤክትሮኒክ የምታቀርበ(ቢ)ው ስምምነት እና የኤሌክትሮኒክ ፊርማ ከግል ፊርማህ(ሽ) ጋር እኩል ተመጣጣኝ መሆኑን እንደተገነዘብክ(ሽ) ይቆጠራል።